http://www.freebirtukan.org
619.597.1086
PO Box 3158, Cypress, CA 90630

# Free Birtukan and All Prisoners of Conscience in Ethiopia

**በአገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ  ለምትኖሩ የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን !**

**እንኳን ለአዲሱ አመት አደረሳችሁ!**

**ዉድ ኢትዮጵያውያን ፣**

**በዚህ አዲስ አመት ሁላችንም በየቤታችን፤ የአዲስ አመት ድግስ ለማድረግ ስንዘጋጅ፣ ሴት ልጆቻችን አበባየሆይ ለመዝፈን ሲቧደኑ፣ ወንጀል ሳትሰራ፣ ፍትህ በሰበከች እንደወንጀለኛ፣ ለሰላም በቆመች እንደ አመጸኛ፤ እዉነት በተናገረች እንደ አጭበርባሪ ተቆጥራ፣ በቃሊቲ እሥር ቤት እየተሰቃየችና እየማቀቀች የምትገኝ እህታችን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ አለች። ሴት ልጅዋ ሃሌ ሚደቅሳ፣ እንደ ሌሎች ሴት ልጆች ተደስታ፣  አበባየሆይ ለማለት አልታደለችም። ይህ አዲስ አመት ለወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳና ለቤተሰቦቿ የደስታ ቀን ሳይሆን የጨለማና የሐዘን ቀን ነዉ።**

**ለኛ ሐዘኑ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በመታሰሯ ብቻ አይደለም። የህግ የበላይነትና የዜጎች ሰብአዊ መብቶችም መለጎማቸው ጭምር ነው። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ለሕዝብ ጥቅም፣ ለአገር አንድነት፣ ለፍትህ በመቆሟ ስትታሰር፣ ከጎኗ ተሰልፈን፣ «የርሷ ትግል የኛም ትግል ነዉ፤ የርሷ ራዕይ የኛም ራዕይ ነዉ» ብለን፣ የለኮሰችዉን ችቦ ይዘን፣  ትግሉን በስፋትና በጥንካሬ መቀጠል ይኖርብናል። ውድ ኢትዮጵያውያን ይችን ታላቅ ሴት ለማስፈታት በግልም ሆነ በቡድን ጥረት ለማድረግ በዚህ አዲስ አመት ቃል መግባት ይጠበቅብናል።**

**በዚህ አዲስ አመት፣ በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ ኃይል፣ በአዲስ ቁርጠኝነት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳንና የህሊና እስረኞችን ለማስፈታት የሚደረገዉን ትግል ለመቀላቀል በሙሉ ልብ እንነሳ።**

**ነጻነት የትግል ተሳትፎ ውጤት ነው!**